# "IRS - ቅርስ መጽሄት"

ሙሳ ማርጃንለ
ዋና አዘጋጅ

አዘርባጃን በጥንታዊ ባህል የበለፀገች ታሪካዊ አገር ናት፡፡ አዘርባጃን በዓለም ውስጥ መንግስት ከመሰረቱ ጥንታዊ አገራት መካከል ለምሳሌ መና፣ ሚዲያ አትሮፓቴና፣ አልባኒያ እና መካከለኛው ካውካስስ አስቀድሞ በአዘርባጃን ጥንታዊ መንግስት ተመስርቶ ነበር፡፡

በአዘርባጃን የሚገኙ ታዋቂ ጥንታዊ የአርኪዎሎጂ ዋሻዎች እንደሚያመለክቱት ከሆነ አዘርባጃን የጥንታዊ ስልጣኔ መገኛ አገር መሆኗን ነው፡፡ በዚህች አገር በአንደኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ  የድንጋይ ላይ ጽሁፍ የሚከተለው ተጽፎበት ይገኛል፡፡ "አቬስታ ታዋቂ የድንጋይ ላይ ጽሁፍ ፈጠረ፣ በድንጋዩም ላይ የዞሮዓስተሪያንዝም የጀግንነት ታሪክ" ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ በጥንታዊን የአዘርባጃን ህዝቦች የተሳሉ የድንጋ ላይ ምስሎች በባኩ እና በጂያሚጓ አቅራቢያ በሚገኙ የመስጊድ ቤተ መንገስትና የመኖሪያ ቤት ግድግዳዎች ላይ ምስሎች ይታያሉ፡፡ ይህም ለዘመናት የበርካታ ጎብኚዎችን ትኩረት ሲስብ ኖሯል፡፡ ለምሳሌ በሞሚን ካቱን ናክቺቫን፣ ሻኪካን ቤተ መንግስት፣ በባኩ ሺርቫንሻህ ቤተ መንግስት የሚገኙ የግድግዳ ላይ ጥንታዊ ምስሎች ይጠቀማሉ፡፡

በአንደኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ባታብሪዝ የነበረውን እጅግ ጠቃሚ የባህል ማዕከል ለምሳሌ የካማላዲን ቤህዛድን ባህል መጥቀስ ይቻላል፡፡

በምስራቅ ለተጀመረው ባህል እና የጽሁፍ ግራፊክስ ጥበብ ሱልጣን ሙሀመድ፣ አሚር ሰይድ አሊ እና ሌሎች በርካቶች በጥበቡ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አድርገዋል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በአዘርባጃን ለተጀመረው የጥበብ ማበብ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የአዘርባጃን ኪነጥበብ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ትልቅ ደረጃ ላይ እና ብረታ ብረት ምርት፣ የጌጣጌጥ ጥበብ ከፍተኛ ደረጃ ላይ  ደርሷል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በአለማችን በሚገኙ እጅግ የተከበሩ ሙዚየሞች የሚገኙት የጥበብ ስራዎች በአዘርባጃንውያንን ጥበበኛ እጆች የተሰሩ የጥበብ ስራዎች ናቸው፡፡

ከታዋቂ የአዘርባጃን ሳይንቲስቶች፣ ፀሀፍት፣ አርቲስቶች፣ ሙዚቀኞች መካከል ኒዛሚ፣ ሃራኒ፣ ፊዚሊ፣ ናሲሚ፣ ካታይ፣ ናታቫን፣ ጃሊል ማማድጉ ሉዛድ፣ ሁሴን ጃቪድ፣ ዩሱፍ ማማዲሊዮቭ፣ ዚያ ቡንያ ዶቭ፣ ኡዜር ራዲ ኪቤኮቭ፣ ጋራ ጋራዮቭ፣ ካርተር ባህሉልዛድ፣ ቡልቡል፣ ራሺድ ቤቡዩቭ እና ሌሎች በርካቶች የአለም የባህል ጀእና ሳይንስ ጠቢባን መካከል  የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

"አይአርኤስ" ጋዜጣ ስለ አዘርባጃን ህዝቦች ታሪክ እና ባህል ዙሪያ መረጃ ይሰጣል፡፡ ለወደፊቱ ስለ አዘርባጃን አዳዲስ መረጃዎችን እናስነብባችኋለን፡፡